
# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

11



መስከረም ፩—፲፱፻፸፬ ዓ. ም.

## ለውይይት መነሻ

**አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፬ ጀምሮ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።**

# የባሪያ ሥርዓተ ማኅበር

( ካለፈው የቀጠለ )

፯ኛ ትምህርት—ከን. ዓ.

የባሪያ ሥርዓት የሚባለው የጋርዮሽ ሥርዓት በተፈጸመ ማግሥት ከሰማይ ዱብ ብሎ የተመሠረተ ሥርዓት አይደለም ። የተጠነሰሰውና መልክ እየያዘ የመጣው በጋርዮሽ ሥርዓት ማኅጸን ውስጥ እንደሆነ ግልጽ ነው ። ይህም ሁኔታ በጋርዮሽ ዘመን መጨረሻ ላይ ከቀድሞው በበለጠ ፍጥነት የባሪያ ገዥዎች መደብ እየተጠናከረ ሲሔድ ነው የባሪያ ሥርዓት እያደገ የሔደው ። በጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥ መስፋፋትና ማደግ የጀመሩት የምርት ኃይሎች በባሪያ ሥርዓት እጅግ ከፍ እያሉና እየተራቀቁ ሔዱ ። ከብት እርባታና የእርሻ ሥራ በሰፊው ተጀመረ ። የሥራ ክፍፍል እያደገና የአሠራሩም ዘዴ ከቀድሞው እየተራቀቀ ሔደ ።

በዚህ ሁሉ የተነሣ በተሻሻሉት የምርት መሣሪያዎች እየሠሩ በብዛት ለማምረት ተቻለ ። በምርት ኃይሎች ማደግ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ሳይሠሩ በምቾት ለመኖር ቻሉ ። የባሪያ ጉልበትም ^ዚህ እጅግ አመቺ ሆነ ።

በጦርነት የተማረኩ ሁሉ ለጦር አለቆችም ለሀብታም ቤተሰቦች በባርነት እንዲገቡና እጅግ አሠቃቂ በሆነ የብዝበዛ ቀንበር እንዲሠሩ ተገደዱ ። አንዳንድ ነፃ ቤተሰቦችም ችግር ላይ ሲወድቁ ከሀብታሞቹ ይበደሩ ስለነበር መክፈል ሲያቅታቸው ዕዳቸውን በጉልበታቸው ለመክፈል በባርነት ይገቡ ጀመር ።

በዚህ መሠረት የባሪያ ጉልበት የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚ መሠረት ሆነ ። ምርትም እጅግ ከፍ ከማለቱ የተነሣ በቀጥታ ከምርት ሥራ ጋር ሳይሳተፉ ምርምርና ጥናት ለማድረግ አንዳንድ ሰዎች ዕድል አገኙ ። የመጀመሪያው የሥራ ክፍያ በአራሽና በከብት አርቢ ሲሆን ፤ ሌሎችም የሥራ ክፍፍል ነበሩ በዚህ ጊዜ ደግሞ ከምርት ተግባር በቀጥታ ሳይሳተፉ አንዱ ያፈራውን ወደሌላ በማዳረስና ሩቅ አገር እየተዘዋወሩ በመሸጥና በመለወጥ መክበር የጀመሩ ነጋዴዎች ተስፋፉ ። ለዚህም ንግድ እንዲያመች ቀድሞ ዕቃ በዕቃ ይደረግ የነበረው ለውጥ ዛሬ ልዩ ልዩ መልክ ባለው ገንዘብ ለሚደረገው ልውውጥ ቦታውን እየለቀቀ ሔደ ።

የባለእጆች ሥራ መስፋፋትና ንግድም ከነሱው ተከትሎ ማደግን ምክንያት በማድረግ በተለይ ንግድ የሚያደራባቸው ከተማዎች ማደግና መስፋፋት ጀመሩ ። በነዚህ ከተማዎችም ውስጥ በባሪያ ጉልበት በመጠቀም ሀብታም ነጋዴዎችና ባሪያ ገዢዎች ታላላቅ ቤተ መንግሥቶችን ፤ ሐውልቶችን ፤ የስፖርት ሜዳዎችን ፤ መናፈሻዎችን በማሠራት እንደዛሬው ቴክኒክ ባልነበረበት ወቅት ፤ የብዙ ሺህ ባሮችን የተቀናበረ ጥረት የሚጠይቁ ታላላቅ ሥራዎችን ለማሠራት ተቻለ ። ከነዚህም ለምሳሌ ፒራሚዶችን ፤ ዩቻይናን ግንብና እንደዚሁም በእኛ አገር በባሪያ ሥርዓት ላይ ተመሥርቶ ብዙ ቅርሶችን ጥሎ የሔደውን የአክሱምን መንግሥትና ሐውልቶችን እስከ ዛሬ ምስክር ሆነው ወጥተዋል ።

ይህ ሁሉ ከፍተኛ እድገት እንዴት ተቻለ ? ይህ የሆነው ጥቂት ሰዎች በብዛት የሚማረኩና የሚገዙ ባሪያዎችን ጉልበት ኢሰብአዊ በሆነ ብዝበዛ እስከ ጉልበታቸው መጨረሻ ጠብታ ድረስ ማሠራት በመቻላቸው ነው ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ የነበረውን የምርት ግንኙነት ብንመለከተው እጅግ የተዛባ ሆኖ እናገኘዋለን ። «አሠሪው» ሙሉ በሙሉ የምርት መሣሪያዎች ባለቤት ነው ። ከመሣሪያዎችም አልፎ በሠራተኛውም ላይ የባለቤትነትና የፈላጭ ቆራጭ መብት አለው ። ባለቤት ባሪያውን መሸጥ ፤ መለወጥ ፤ በስጦታ ማበርከት ፤ መግደል ፤ ማውረስ ፤ ማሠር ባጭሩ እንደሰብአዊ ፍጡር ሳይሆን «እንደሚናገር መሣሪያ» በሚቆጠረው ባሪያ ላይ ሙሉ የሆነ ፈላጭ ቆራጭነት ነበረው ።

የባሪያ አገዛዝ ሥርዓት የመጀመሪያው በመደቦች ክፍፍል ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ፤ ከሁሉም ኢሰብአዊ የሆነ ሥርዓት ነበር ። እንግዲህ ጥያቄው ሰው እንዴት ብሎ ይህንን ግፈኛ ሥርዓት አሜን ብሎ ተቀበለ የሚለው ነው መልሱም «አሜን» ብሎ አልተቀበለም ። የጋርዮሽ ሥርዓት ፈርሶ ኅብረተሰቦች በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች ከተከፈሉ ወዲህ በሁለቱ መካከል የማያቋርጥና አንዴ እየቀዘቀዘ አንዴም እየከረረ ፤ አንዴ ውስጥ ውስጡን ፤ አንዴ ደግሞ በይፋ፤ አንዴ በቀጥታ ሌላ ጊዜ ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገዶች የሚካሔድ ትግል አለ ። ለዚህ ትክክለኛ ቦታውን በመስጠት ነው ማርክስና ኤንግልስ «እስከ ዛሬ ድረስ ያለው የሰው ዘር ታሪክ ከጋርዮሽ ሥርዓት በስተቀር የመደቦች ትግልና ታሪክ ነው» ብለው የጻፉት ። ይህንን መደቦችም የመደቦች ትግል በሚለው ርእስ ውስጥ በሰፊው እንመለስበታለን ።

አሁን ግን በቦታው ለማስታወስ ያህል እዚህ ላይ ጠቀስ አድርገን ማለፍ ያለብን የመንግሥት ጉዳይ አለ ። ማንኛውም የሚያሳብር አእምሮ ያለው ሰው እየሠራ ለሰው ማስረከብን በደስታ የሚቀበል የለም ። መሸጥን ፤ መለወጥን ፤ ከአገር ፤ ከቤተሰብ ተነቅሎ ለዘለዓለም በማያውቁት አገር ተሸጦ ተለውጦ ከእንስሳት እኩል ተቆጥሮ መኖርን ካልተገደደ (በችግር ፤ በሕግ ፤ በጦር) የሚቀበል የለም ። የባሪያ ገዢ መደቦች ይህንን ሐቅ ጠንቅቀው በማወቃቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የብዝበዛውን ሥርዓት የተከተሉትን ያህል ለመጀመሪያ ጊዜ በሰው ዘር ታሪክ መንግሥት የሚባለውን የማስገደጃ ድርጅት አቋቋመ ። ይህ መንግሥት የሚባል የማስገደጃ ድርጅት ከሰማይ ዱብ ያለ ነገር ሳይሆን ኤንግልስ እንዳለው « እንዲያውም አንድ የተወሰነ እድገት የደረሰው የራሱ የኅብረተሰቡ ውጤት ነው ። መንግሥት ሲቋቋም ኅብረተሰቡ ፈጽሞ የማይወጣው ቅራኔ ውስጥ መግባቱንና በምንም ዓይነት ሊታረቁ በማይቻሉና ሊከላከላቸው በማይችላቸው ቅራኔዎች ውስጥ መግባቱን ኅብረተሰቡ አመነ ማለት ነው ። ነገር ግን እነዚህ ተቃራኒ መደቦች በማያልቅ ትግል ውስጥ እነሱን ኅብረተሰቡንም ይዘው እንዳይጠፉ ከኅብረተሰቡ በላይ በመምሰል ጠቡን ለማቀዝቀዝ ፤ ከደንብ ውጭ እንዳይሆን ለመጠበቅ አንድ ሥልጣን አስፈለገ ። ይህ ከኅብረተሰቡ ውስጥ የወጣም ቢሆን እያደር ለኅብረተሰቡ እንግዳ እየሆነ የሚሔደው ሥልጣን መንግሥት ነው ።

በባሪያም ሥርዓት ሆነ ከዚያም በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ ለወደፊትም ከሕዝቡ የተለየ ሠራዊት ፖሊሲ ፤ ወህኒ ቤት ፤ ዳኛ . . . ያሉት የማስገደጃ መሣሪያ መንግሥት ተግባር የአንድን መደብ ወይም የተወሰኑ ሰዎችን ጥቅም በሌሎች መደቦች ላይ ለማንገሥ መሆኑን የሶሻሊዝም ፈላስፋዎች እየደጋገሙ አስረድተዋል ። በዚህ መሠረት የባሪያ ሥርዓት መንግሥት ተበዝባዥ ባሪያ ቦታውን ሳይስት እንደገዛ የሚያስገድድ ለባሪያ ገዥዎች ጥቅምና በነሱው የቆመ መንግሥት ነው ።

በዚህ ሁሉ አንፃር የኢትዮጵያን ሁኔታ ብንመለከት የአክሱም መንግሥት በባሪያ ሥርዓት ላይ የቆመ እንደነበረ የሚያስረዱ ብዙ መረጃዎች አሉ ። የኢትዮጵያን ታሪክ በዚህ በክፉና በደጋግ ነገሥታት መውጣትና መውረድ ፤ በግለሰቦች ጀግንነት ፤ ስሕተት ፤ እብሪት ፤ ነገር ፍቅር ሳይወሰኑ በዚህ በስልተምርቶች መለዋወጥ ታሪክ አጥንቶ ማቅረብ ተራማጅ የታሪክ ምሁራን ተግባር ስለሆነ እዚህ በዝርዝር ለመግባት አይችልም ። በአጠቃላይ ሲታይ ግን የአክሱም መንግሥት ከተመሠረተበት ወቅት አንሥቶ የተጨቆኑ ሕዝቦችን አስነስታ በመምራት ዮዲት እስካፈራረሰችው ድረስ የሚያሳየው መልኩ ሁሉ በባሪያ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያስረዳል ።

በባሪያዎች ላይ የሚደረገው ብዝበዛ እየጨከነና እየከፋ እንደመሄዱ መጠን በዚያው ልክ ደግሞ የሚካሔደው የመደበኞች ትግል ከመጠን በላይ እየተፋፋመ ሔደ ። እስከዛሬም ቢሆን ነፃነት ተጋድሎ በምሳሌነት የሚጠቀሰውና ከሁሉ ዝናን ያተረፈው የባሪያዎች አመጽ ለምሳሌ ስፖርታከስ በሚባለው ባሪያ የተመራው ሲሆን በእኛም በኢትዮጵያ የሂድን እንደሆን አሁንም እንደማስፈራሪያ እየተጠቀሰች የምትቀርብልን « ዮዲት ጉዲት» የተባለችው በአክሱም የባሪያ አገዛዝ ሥርዓት ታፍነው የተያዙትን ጭቁን ሕዝቦች አስነስታ በመደብም ላይ የነበረውን የአክሱም ግዛት ብዙ ምሬት

ያበሰረች የነፃነት ትግል መሪ ነበረች ።

ነገር ግን እነዚህ የጭቁን ሕዝብ አመፆች ከባሪያ ሥርዓት ኢኮኖሚ መበስበስ ጋር በጥብቅ የተያያዙ እንደነበሩ ግልጽ ነው ። በዚህ ዘመን የምርት ኃይሎች እጅግ ተሻሽለው ፤ ንግድ ዳብሮ ከተማዎች ተስፋፍተው ኢኮኖሚው በከፍተኛ ደረጃ ላይ ቢገኝም ቅሉ የምርቱ ሁሉ ዋና መሠረት የሆነው ሰው በባርነት እንደሚናገር መሣሪያ ተቆጥሮ መዋረዱ ፍጹም ለእድገት አዳጋች እየሆነ መሔዱ ግልጽ ነው ። በተሻሻሉት መሣሪያዎች ሠርቶ በብዛት ማምረት ሲቻል « ሺህ ቢታለብ ያው በገሌ » እንዳለችው ድመት ባሪያው ጠንክሮ ሠርቶ ምርቱን ቢያሻሽል ከዚያች ከዕለት ጉርሱ ሌላ የሚያገኘው እንደሌለው ሲያውቅ መለገሙ አልቀረም ። ለምሳሌ በሮማ በሰፋፊ እርሻዎች ላይ ተሰማርተው የሚሠሩ ባሮች እንኳን እየተሻሻሉ በሚሔዱ ቴክኒኮች ተጠቅመው ምርት ሊያሳድጉ ይቅርና እንዲያውም ምርቱ እየቆረቆዘ መሔዱ ይነገራል ። በዚህን ጊዜ ባሪያ እንዳይለግም በማሰብ አሠሪዎች እጅግ የተወሳሰበና ብዙ ኪሣራም የሚጠይቅ የቁጥጥር ዘዴ በእርሻዎቻቸው ላይ ለመትከል ሞከሩ ። ነገር ግን በሠራተኞቹ ላይ እንዲህ ከፍተኛ ወጭ እየወጣ የሚደረገው ቁጥጥር ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ ስላመዘነ ባሪያው ራሱ አስቦ የሚሠራበት ለዚህ ደግሞ ጠንክሮ ከሠራና ምርት ከጨመረ የሱም ደረጃ በዚሁ ልክ ከፍ የሚልበት የማፍሪያ ግንኙነት መፍጠርና ኅብረተሰቡን ወደፊት ማራመድ አስፈላጊ ሆነ ።

እንግዲህ የባሪያ ሥርዓት ውስጣዊ ቅራኔዎች አለቅጥ ተፋፍመው ባሪያዎች እየደጋገሙ በማመጻቸውና በኢኮኖሚውም በኩል ኅብረተሰቡን ወጥረው ከያዙት ቅራኔዎች ለማውጣት በተሻሻሉት የምርት ኃይሎች የተሻሻሉ የምርት ግንኙነቶች አስፈላጊ በመሆናቸው የባሪያ ሥርዓት ፈንድቶና ተሽሮ በሱ መቃብር ላይ ታዳጊውና የተሻለው ባርነት ቀርቶ ጢሰኝነት የተተከለበት የፊውዳል ሥርዓት ተተካ ።

## የፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር

የባሪያ ሥርዓት የኢኮኖሚው መሠረት ተናግቶ እጅግ በተደጋገመ የባሪያ አመፆች ተዳከመ ። በያለበት የዚህ ሥርዓት መውደቅ አትርፎ የሄደው ለተወሰነ ጊዜ ከፍተኛ ውኅርንብር መፍጠርን ፤ ጠቅላላ የሆነ የፀጥታ መታወክ ፤ ሽብርንና በዚሁ ሁሉ ውካታ መሐል ሰላምና መብቱን የተነፈገው ገበሬ በረጋ መንፈስ መሥራት ባለመቻል የምርት መውደቅንና ጠቅላላውን የኅብረተሰቦችን መፈራረስ ነው ። ወደፊት እንደምናያቸው የከበርቴና የሶሻሊስት አብዮቶች አንዱ ሥርዓት ሲወድቅ ሌላው ሥርዓት በመጠነኛ ጊዜ ተተክቶና መሥመር ይዞ የኅብረተሰቡን ዕድገት የተፋጠነ አላደረገውም ። የባሪያ ሥርዓት በፈራረሰበት ቦታ ሁሉ ፊውዳሊዝም መልክ የሚሰጡትን ጠባዮች ይዞ ብቅ እስኪል ድረስ በጨለማ ውስጥ የተካሔደው አብዛኛውን ጊዜ እንደባሪያ ሥርዓት እንኳን በጽሑፍ ለታሪክ ያልተቀመጠ ብዙ ነገር ተካሂዷል ።

ለምሳሌ የኢትዮጵያን ታሪክ ብንወስድ በባሪያ ሥርዓት ላይ የተመሠረተው የአክሱም ግዛት ምን ያህል ጠባብ እንደነበረ በብዙ መረጃዎች ማግኘት ይቻላል ። እየተዳከመም መጥቶ ግብዓተ መሬቱ በታላቋ የነፃነት ተጋዳይም « በዮዲት ጉዲት » በተመሩ ጭቁን ሕዝቦች አመፅ የተፈጸመ መሆኑ ይታወቃል ። ከዚያ ወዲህ ላሉት ቢያንስ ሁለት መቶ ዓመታት አክሱምን ስለተካው ገና በእንጭጭ ላይ ያለው ፊውዳል ሥርዓት ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም ። ብዙዎች ይህንን ዘመን የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን ያሉት ለዚህ ነው ። በአውሮፓም ቢሆን « ዘዳርክ ኤጀስ» የሚባለው ይኸው ዓይነቱ ዘመን ነው ።

በአጠቃላይ የባሪያ ሥርዓት እየፈራረሰ ሲሄድ የፊውዳሉ ሥርዓት መልክ እየያዘ የመጣበትን አረማመድ ግን ለመታለም ይቻላል ። በተነሣው ሁከት ሳቢያ በየመንደሩ መሣሪያ ያለው የመንደር አምባ ገነን በዛ ። አካባቢውን መረበሽ ፤ መዝረፍ ፤ ፀጥታ መንሳትና መሣሪያ ለሌለው ሁሉ እርዳታን የሚነሳ ለሥራ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጠረ ። መሣሪያ ካለው ማንም ተነሥቶ አስገብራለሁ ይላል ።

« ባለጉልበት ሂዶ ያስገብራል የትም » መሬት የሁሉ ናት ባለቤት የላትም ተብሎ የተተረተው ለዚህ ጊዜ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል ። ፀጥታ አግኝቶ ሠርቶ ለማደር የፈለገ ሁሉ እንግዲህ የቀረው ምርጫ ለባለጉልበት በጥገኝነት መግባትና በሱ ጥበቃ ሥር ከምርቱ እያካፈለ መኖር ሆነ ። በዚህ መልክ ነው ። «ጠብቀኝ አገለግልሀለሁ ቱመ ፕሮቴኸ ኸታሰር» የሚለው የፊውዳል ሥርዓት መሠረታዊ ውልና የምርት ግንኙነቶች አውታር ሆኖ እስከዛሬ የመጣው ባለጉልበቱ በዚህ መልክ ጥገኞቹን ለመጠበቅ ሠራዊቱ ለማስተዳደር ደግሞ ዳኛ ፤ ግብር ሰብሳቢ ፤ ፀጥታ ጠባቂ እያለ መሾምና ግዛቱን ማስፋፋት የጀመረው የጉልበት መዳበር በይበልጥ የግዛት መስፋፋትን ስለጠየቁና ስላስቻለ ባለጉልበቱ ባላባት በሚስፋፋበት ሁሉ የሱን ታማኝ አሽከሮች በአስተዳዳሪነት ሾመበት ። ቀስ በቀስ በባለጉልበቱ አካባቢ ሥር መስደድ የጀመሩት ታማኞቹም ቤተሰቡ መሳፍንት ፤ መኳንንት እየተባሉ መልክ የያዙ የገዥ መደብ ቦታ ለመያዝ በቁ ከዚህ ተከታትሎ ባለንበት ንጉሥ የተቀሩት መሳፍንትና መኳንንት ስፍራቸውን ለማወራረስ ለልጅ ልጅ የማስተላለፍ መብት ስለታወቀላቸው የፊውዳል ሥርዓትን አይነተኛ የሚያደርገው ሌላ ጠባይ በመያዙ ይኸውም የመሳፍንት ልጅ መስፍን ፤ የጢሰኛ ልጅ ጢሰኛ ፤ የባለእጅ ልጅ ባለእጅ በሚል ዘይቤ የሥርዓቱ መሠረት የረጋ መልክ መስጠት ነው ። ስለዚህ ጉዳይ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የጻፉትን ብንመለከት ምንም እንኳን በዚህ መልክ እየተደላደሉ ቢሄዱም በያለበት ያሉት አምባገነንነትና ባለጉልበቶች እርስ በእርሳቸው መዋጋትም ግዛታቸውን ለማስፋፋት ይጥሩ ስለነበረ የፊውዳል ዘመን ታዳጊ በሆነበት ወቅት ጦርነት አያጣውም ነበር ። ገቢ ሊያድግ የሚችለው እስከዚህም እውቀትን አዳብሮ ምርትን በማሳደግ ሳይሆን ብዙ ሰው ፤ ብዙ ግዛት ማስገበር ሆኖ የሚታይበት ወቅት ስለነበረ አንዱ ባላባት ሌላውን ባላባት አንዱ ንጉሥ ሌላውን ንጉሥ ለማስገበር ከባላባትነት አልፎ የባላባቶች ባላባት ፤ ከንጉሥነት አልፎ የነገሥታት ንጉሥ መሆን ለዘረፋ ይበልጥ የሚያመች በመሆኑ በዚህ የፊውዳል ሥርዓት የዕድገት ደረጃ ለወረራና ለማስገበር ዓላማ ባላቸው ጦርነቶች እጅግ ያመቸ ወቅት ነበር ። ይህም በታሪክ ውስጥ «ፊውዳል ደሳዩኔቱ» «ወይም « የፊውዳል ክፍልፍል » አገዛዝ የሚባለው ሲሆን በሀገራችን የፊውዳል ሥርዓት አስተዳደግ ውስጥ «ዘመነ መሳፍንት» እየተባለ የሚጠራውን ዘመን ያመለክታል ።

በኢትዮጵያ ነገሥታት ጦረኛ የሆኑት አብዛኞቹ ከጦር ሜዳ ጦር ሜዳ ሲንከራተቱ ቋሚ ዋና ከተማ እንኳን ሳይኖራቸው ዕድሜያቸውን ያሳለፉት አንዱን ባላባት «ሲያረጋጉ» ሌላው «እየሸፈተ» በዚሁ የግዛት መስፋፋትና መጠበቅ ዘመቻ መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህ የፊውዳል የእድገት ዘመን ግን ቀስ በቀስ እየዳበሩ የሚሔዱት የምርት ኃይሎች በተለይም በሰላም ጥቅሙን ለማዳበር ለሚፈልገው ነጋዴ ፤ ከበርቴ ፤ ባለእጅ ፤ አልሙች በማለቱ ፤ በተለይም በፊውዳሎቹ ትርምስ ፀጥታና ሰላም ተነሥቶ ዘረፋ አስመርሮት መኖር ላቃተው ገበሬ የሚያስመርር በመሆኑ እነዚህን ተቀናቃኝ ኃይሎች ሁሉ በአንድ ግዛት ሥር አጠቃሎ በፈላጭ ቆራጭነት እየገዛ ጭጭ የሚያደርግና ለሥራ አመች የሆነ አካባቢ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ የፊውዳል ዘመን ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ የፈላጭ ቆራጭ የንጉሠ ነገሥት አገዛዝ ቀስ በቀስ ተመሠረተ ። በኢትዮጵያ ለምሳሌ ፊውዳሊዝም ትክክለኛ የእድገት አቅጣጫውን በመቀጠል ከተበታተነው «ዘመነ መሳፍንት» ወደተጠቃለለው የንጉሠ ነገሥት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እንዲያድግ ለሚደረገው ትግል ቴዎድሮስ ዓይነተኛ ሚና የተጫወቱ ናቸው ። የሳቸውም አነሣሥና « ዘመነ መሳፍንት » የሚባለው የዝቅተኛ የፊውዳል ሥርዓት ደረጃ ማክተም በዚህ የማንኛውም ፊውዳል ኅብረተሰብ ታሪክ በሚከታተለው እርምጃ አንፃር መታየት አለበት እንጂ ፤ ታሪክ ጸሐፊዎቻችን እንደሚሉት ዘመነ መሳፍንት የተፈጸመው አማታቸው የኮሶ ስንብት አንድ እግር ሥጋ ስለላኩላቸው ተቆጥተው በመሸፈታቸው ነው የሚለው ፈጽሞ ተቀባይነት አልነበረውም እጌ ቴዎድሮስ ምናልባት ሙሉ በሬ ቢላክላቸው ፤ ወይም ከአማታቸው ከራስ አሊ ጋር የሠመረ ግንኙነት ቢኖራቸው ኖሮ እርግጥ አይሸፍቱ ይሆን ይሆናል ። ነገር ግን መቶ ዓመታት ለሚሆን ጊዜ ሀገሪቷን ኃይለኛ ትርምስ ውስጥ ጨምሮ ፀጥታ ነሥቶ ፤ ለንግድ፤ ለግብርም ፤ በባለእጅ ያስቸገረው የምርት ኃይሎችን አፍኖ የያዘው ዘመነ መሳፍንት በስብሶ መወገጃው ጊዜ ነበርና ፤ የሱ መፈጸም የጠቅላላው የምርት ኃይሎች እድገት የሚጠይቀው ታሪካዊ ግዴታ ነበርና ቴዎድሮስ ወይንስ ሌላ ሰው ተነሥቶ ሕዝቡን ለዚህ ተግባር ያሰልፍ እንደነበረ ግልጽ ነው ።

እንግዲህ እስቲ ይህንን በዚህ እንተውና በፊውዳል ዘመን የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች እንዴት እንደነበሩና እያደጉም ሔደው እንዴት ከዚህ ሥርዓተ ማኅጸን የካፒታሊስት ሥርዓት ተጠንስሶ እንደወጣ እንመልከት ።